# ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

## የበዓላት ትንሣኤ (ሰንበታት) ሥርዓተ አምልኮት (በዓለ ኃምሳ)

ክርስቶስ ተንስአ እሙታን
በዐቢይ ኃይል ወስልጣን
አሰሮ ለሰይጣን
አግአዞ ለአዳም
ሰላም እምይእዜሰ
ኮነ ፍስሃ ወሰላም

ክርስቶስ ከሙታን ተነሳ
በታላቅ ኃይልና ስልጣን
ሰይጣንን አሰረው
አዳምን ነጻ አወጣው
ከዛሬ ጀምሮ
ደስታና ሰላም ሆነ

## የትንሣኤ ሰሞን

በዓለ ኃምሳ የሚባለው ከትንሣኤ እስከ በዓለ ጰንጠቆስጤ (በዓለ ጰራቅሊጦስ) ድረስ ያለው ኃምሳ ዕለት ነው። በዚያ ወቅት ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስን ትንሣኤ ታከብራለች። በክርስቶስም ያገኘችውን እረፍት ነፍስ በምልአት ትሰብካለች። እረፍተ መንግሥተ ሰማያትን ታስባለች፤ በእነዚህ ዕለታት ዓርብ፣ ረቡዕ አይጾሙም፤ ቀኖና ለተነሳህያን አይሰጥም፤ በስግደት፣ በድካም፣ በትምህርት፣ የሚኖሩ ሁሉ በእረፍት ያሳልፉታል። በዚህ ወቅት ቅዳሴ፣ መዝሙር ድካም የማያስከትል ሥርዓተ አምልኮት ይፈጸማል። ይህ ሁሉ የሚሆነው በክርስቶስ እረፍተ ነፍስ አግኝተናል።




ጌታ የትንሣኤያችን በኵር ነው። እኛም ከተነሳን በኋላ እግዚአብሔር ረሃብ፣ ጥም፣ ድካም፣ ሕመም፣ ፈተና፣ ሞት፣ ፈታኝ፣ መቃብር፣ ብልየት፣ ልደት፣ ልህቀት፣ ኃይለ ዘር፣ ኃይለ ንባብ፣ ኃይለ እንስሳ የሌለበትን፣ ሥርዓተ ምድር አልፎ በአዲስ ሥርዓተ-ሕይወት የምትመራውን እረፍተ መንግሥትን እንወርሳለን ለማለት ነው። ቀኖና የሚይሰጠው በሥጋም ሆነ በነፍስ ከመግደል ጌታ ነጻ ያወጣናል፣ ባለመበደል በአፋችን ምስጋና መልቶ ሕይወታችን ከበደል ተለይቶ የምንኖርበት ዘመን ይመጣል። በትንሣኤው በእርገቱም ጽድቅና ጸጋ ሕይወት ተሰጥቶናል። ከተዋርዶ ነፍስ ድነናል ለማለት ነው። በአጠቃላይ ድኅነተ ነፍስ፣ ድኅነተ ሥጋ በኢየሱስ ክርስቶስ ተሰጥቶናል፤ እረፍተ መንግሥተ ሰማያት የዘለዓለም ሕይወት ተዘጋጅቶልናል ማለት ነው።

### እሑድ የአንደኛ ሳምንት

እሑድ በዓለ ትንሣኤ ሲሆን ጌታችን ከሙታን ተለይቶ መነሳቱን፣ ሞትን በሞቱ ድል መንሳቱን፣ ሙስና መቃብርን (በመቃብር ፈርሶ በስብሶ መቅረት) መጥፋቱን፣ በሞቱ በመስቀሉ ያዳናቸውን በትንሣኤው ማጽደቁን፣ በዝግ ቤት ገብቶ በፍርሃት ለነበሩት ሐዋርያት ሰላምን እርቅን መስበኩን ቤተ ክርስቲያን ታስባለች።

### ሰኞ ማእዶት

ማእዶት ማለት መሻገር ማለት ሲሆን፤ በዚህ ቀን ቤተ ክርስቲያን ነፍሳት በክርስቶስ ምትና ትንሣኤ ከሞት ወደ ሕይወት፣ ከሐሳር ወደ ክብር፣ ከሲኦል ወደ ገነት መሻገራቸውን ፋሲካችን ክርስቶስ መሆኑን ታስባለች።

### ማክሰኞ ቶማስ

በዚህ ዕለት ቅዱስ ቶማስ በጦር የተወጋ ጎኑን በሚስማር የተቸነከረ እጁን ካላየሁ አላምንም

# ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

## የበዓላት ትንሣኤ (ሰንበታት) ሥርዓተ አምልኮት (በዓለ ኃምሳ)

ማለቱን፣ ክርስቶስም ቶማስን «ጣትህን ወደዚህ አምጣና በጎኔ አግባው ያመንህ እንጂ ያላመንህ አትሁን አለው፤ ቶማስም ጌታዬ አምላኬም ብሎ መለሰለት። ኢየሱስም ስለ አየኸኝ አምነሃል። ሳያዩ የሚያምኑ ብፁዓን ናቸው አለው።» (ዮሐ ፳፤፳፯-፳፱) ተብሎ እንደተጻፈ። ቶማስ የጌታን ፍቅር ተንበርክኮ ትንሣኤውን የማመኑ ነገር የሚታሰብበት ቀን እንዲሆን ስለተወሰነ ቤተ ክርስቲያን ዕለቱን ቶማስ ብላ ታስበዋለች።

### ረቡዕ አልአዛር

በዚህ ዕለት ትንሣኤና ሕይወት የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ አልአዛርን ከሞተ ከተቀበረ ከአራት ቀን በኋላ ማስነሳቱን፤ ለአይሁድ ቅንአት ለጌታ ሞት ምክንያት ከሆኑት ታላቅ ተአምራቶቹ አንዱ የአልአዛር ትንሣኤ መሆኑን፤ አልአዛርን በብሉይ ሥጋ በአምላካዊ ቃሉ ከመቃብር ያስነሳው ጌታ በሐዲስ ሥጋ መነሳቱን ሞት ይይዘው ዘንድ የማይችል አምላክ መሆኑን፤ እርሱ ለፍጥረት ሁሉ ትንሣኤና ሕይወት መሆኑን፤ የምናምንበትን ሁሉ ትንሣኤ ዘለክብር፤ የማያምኑበትን ትንሣኤ ለዘሐሳር ማስነሳት የሚቻለው ጌታ መሆኑን ቤተ ክርስቲያን ታስባለች (ዮሐ ፲፩ በሙሉ)።

### ሐሙስ አዳም ወይም አዳም ሐሙስ

በዚህ ዕለት ለአዳም የተሰጠው የተስፋ ቃል ስለመፈጸሙ (ዘፍ ፫፥፲፭)። አዳም ከነልጆቹ በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ነጻ ስለ መውጣቱ ይታሰባል።

### ቅድስት ቤተ ክርስቲያን

በዚህ ዕለት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ስለ መመሥረቷ፤ ለቤተ ክርስቲያን እርሱን ስለ እርሷ አሳልፎ ስለመስጠቱና ቤተ ክርስቲያንም የእርሱ አካል ስለመሆኗ (ኤፌ 5፥ሉ1)፤ የነቢያትና የሐዋርያት መሠረት በሆነው በክርስቶስ ላይ ስለ መመሥረቷ፤ መሰብሰቢያዋም ክርስቶስ ስለ መሆኑ (ኤፌ ፪፥፲፱-፳፪) ታስባለች።

በተጨማሪም በደሙ ስለ መታጠቧ (ራዕ ፭፥፱-፲) ከነገድ ከቋንቋ ስለመመረጧ፤ በደሙ ተዋጅታ አንድ መንጋ ስለመሆኗ፤ በሰማይ ሠራዊት በምድር የሰው ፍጥረት ያላገኘችውን ሕይወት በእርሱ ስለማግኘቷ (ራዕ ፭ በሙሉ)፤ በወርቅ በብር ሳይሆን በክቡር በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ስለመዋጀቷ (፩ኛ ጴጥ ፩፥፲፰-፲፱) ከልዩ ልዩ አነዋወር ተጠርታ በእርሱ ላይ ስለመታነጿ (፩ኛ ጴጥ ፪፥፭-፱)፣ .... እያሰበች ቤተ ክርስቲያን የቤተ ክርስቲያንን ሕይወት ትሰብካለች።

### ቅዳሜ ቅዱሳት አንስት

በዚህ ዕለት የክርስቶስን አካል ሽቱ ለመቀባት ፍርሃታቸውን በክርስቶስ ፍቅር ለውጠው በጋለ ፍቅር አካሉን መፈለጋቸውን፤ ወደ መቃብሩ ሲመላለሱ ማደራቸውን፤ ማርያምም ትንሣኤውን ቀድማ ስለማየቷ፤ ሴቶችም የመላእክትን ራዕይ ስለማየታቸው ቤተ ክርስቲያን የምታስተምርበት ዕለት ነው። (ማቴ ፳፰፥፩-፲፭ ። ማር ፲፮፥፩-፰ ። ሉቃ ሉ፳፬፥፩-፲፪ ። ዮሐ ፳፥፩-፲፰)።

ክብርና ምስጋና ለአምላካችን ለእግዚአብሔር ይሁን ... አሜን።